Issue No. 44
January -April 2011

# FSS Update

Forum for social studies
ፎረም ፎር ሶሻል ስተዲስ

An e-newsletter
to facilitate networking and information exchange among CSOs and researchers

## In this issue:

የጎዳና ተዳዳሪ ህጻናት አጠቃላይ ሁኔታ በኢትዮጵያ

☼☼☼

የአየር ንብረት ለውጥ፤ የውሃ ሐብትና የኢነርጂ ልማት በኢትዮጵያ

☼☼☼

የፎረም ፎር ሶሻል ስተዲስ አመታዊ ጠቅላላ ጉባኤውን አካሄደ

☼☼☼

National Workshop on Urban Climate Change

☼☼☼

UN Climate Talks (Bangkok, 3-8 April 2011)

☼☼☼

# የጎዳና ተዳዳሪ ህጻናት አጠቃላይ ሁኔታ በኢትዮጵያ

ፎረም ፎር ሶሻል ስተዲስ "ባህልና ልማት" በሚል ዐቢይ የመወያያ ርዕስ ያዘጋጀው አስራ ሁለተኛውና የመጨረሻው የውይይት መድረክ "የጎዳና ተዳዳሪ ህፃናት አጠቃላይ ሁኔታ በኢትዮጵያ" በሚል ርዕስ ጥር 27 ቀን 2003 ዓ.ም በግዮን ሆቴል ተካሄዷል፡፡ በዕለቱ ለውይይት መነሻ የሆነውን ጥናታዊ ፅሁፍ ያቀረቡት በፎረም ኦን ሰስተነብል ቻይልድ ኢምፕሩቭመንት (Forum on Sustainable Child Improvement) የፕሮግራም ዳይሬክተር የሆኑትና በመስኩ የብዙ አመት ልምድ ያካበቱት አቶ አበባው በቀለ ናቸው፡፡

የዕለቱን ውይይት የመሩት ዶ/ር መለሰ ጌጡ (ከአ.አ.ዩ) ናቸው፡፡ ለውይይት በቀረበው ፅሁፍ ላይ አቶ ፋሲል ወ/ማርያም ሙያዊ አስተያየታቸውን አቅርበዋል አቶ ፋሲል በህፃናት ላይ ትኩረት አድርጎ የሚሰራው ኦክ ፍውንዴሽን (OAK Foundation) የምስራቅ አፍሪካ የፕሮግራም አስተባባሪ ሲሆኑ የፎረም ኦን ስትሬት ችልድረን (Forum on Street Children) መስራች አባልና እ.ኤ.አ ከ1995 -2003 የድርጅቱ ስራ አስፈፃሚ ዳይሬክተር በመሆን ያገለገሉ ናቸው ፡፡




ስብሰባው ከመጀመሩ ቀደም ብሎ የፎረም ፎር ሶሻል ስተዲስ ሥራ አስፈጻሚ ዲሬክተር ዶ/ር ምህረት አየነው የውይይቱን መጠናቀቅ አስመልክተው ንግግር አድርገዋል፡፡ በንግግራቸው ኤፍ.ኤስ.ኤስ. ከተቋቋመበት ዓላማዎች አንዱ የአንድ ትውልድን የዳበረ ልምድ ፣ ተሞክሮና እውቀት ወደሚቀጥለው ትውልድ ማስተላለፍ መሆኑን ገልፀዋል፡፡ በአግባቡ ወደሚቀጥለው ትውልድ ሳይተላለፍ ቢቀርና የመቋረጥ ሁኔታ ቢፈጠር በተቋማት ዕድገት ላይ አሉታዊ ተፅእኖ ማሳደሩ እውን ነው፡፡ ይህንን በመረዳት አንጋፋው ትውልድ ያካበተውን ክህሎት ለመጪው ትውልድ እንዲያስተላልፍ ለማስቻል፣ ኤፍ.ኤስ.ኤስ «ከድህነት ወደ ልማት ፡- እውቀትን ለትውልድ ማስተላለፍ» የሚል ሕዝባዊ ውይይት ፕሮግራም ቀርጾ ሲንቀሳቀስ እንደነበረ አብራርተዋል፡፡

በርዕሱ አማካኝነት በመንግሥት የልማት ተቋማት፣ በግሉ ክፍለ ኢኮኖሚ፣ በሚዲያ እና በትምህርት ዘርፎች ውስጥ ለብዙ ዓመታት በአመራር ደረጃ ወይም በከፍተኛ ባለሙያነት አገልግለው በጡረታ ላይ የሚገኙ አንጋፋ ዜጎች ተሞክሮዎቻቸውን ለወጣቱና በመካከለኛው እድሜ ላይ ለሚገኘው እንዲያስተላልፉ ተደርጓል፡፡ ከተጉኙ ጠቃሚ ልምዶች በመነሳት «ባህልና ልማት» ያላቸውን ቁርኝት መዳሰስ አስፈላጊ ነው ብሎ የኤፍ.ኤስ.ኤስ ቦርድ ወስኖ ስለነበር በዚሁ ጭብጥ ላይ ተከታታይ ውይይቶችን እውቀትን ለትውልድ ማስተላለፍ ከሚለው ርዕስ ሥር ተከታትሎ እንዲቀርብ መደረጉ ብዙ ጠቀሜታ ተገኝቶበታል፡፡

ኤፍ.ኤስ.ኤስ ጭብጡን ለውይይት ለማቅረብና ፣ አንደኛ ባሕልና ልማት ያላቸውን ቁርኝት ለማሳየት ፣ ሁለተኛ ሀሳቡን ለማስፋፋት፣ ሶስተኛ እስከአሁን ያልተዳሰሱ ከልማት ጋር በጣም የተዛመዱ ማህበራዊና ባሕላዊ ጉዳዮችን፣ ተቋማችን፣ እሴቶችንና ችግሮችን ለመዳሰስ ሰፊ እንቅስቃሴ አድርጓል፡፡ ይህንም ግንዛቤ ውስጥ

Address: FSS, P.O. Box 25864 code 1000, A.A., Tel. (251-11) 629 78 88/ 91,
Fax: (251-11) 629 78 89
Email: fss@ethionet.et Web: www.fssethiopia.org.et

በማስገባት «›ባህልና ልማት» በሚል ርዕስ በተከታታይ ሕዝባዊ ውይይቶች እንዲዘጋጁ ስለተወሰነ ያለፉትን ሁለት ዓመታት የወሰዱ 12 ውይይቶች ተደርገዋል፡፡ የልማትና የባህል ጽንሰ ሃሳባዊ ግንኙነት ዙሪያ፤ ዕድሮችና ሌሎች ልማዳዊ ተቋሞች ለልማት ያላቸውን አስተዋጽኦ በተመለከተ፣ ባህል፣ ስርአተ ጾታና ልማት ፣ ልማትና ስነ-ጽሑፍ፣ ስነስዕልና ስነ ሙዚቃ፣



የሃይማኖት እኩልነት መቻቻልና ልማት፣ እንዲሁም የጐዳና ተዳዳሪ ሕፃናት ችግሮችን በተመለከተ ሰፊና ጥልቅ ውይይቶች ተካሂደው እጅግ ጠቃሚ ልምዶች ተገኝተዋል ብለዋል፡፡

ፎረሙ ለወደፊቱም ቢሆን የሕዝብን ተሳትፎ ለማዳበርና ጠቃሚ እውቀቶችንና ልምዶችን ለማስተላለፍ ይረዳሉ በሚሉ ወቅታዊ ሃገራዊ ጉዳዮች ዙሪያ በተመሳሳይ በምርምር የተደገፉ ህዝባዊ የውይይት መድረኮችን እንደሚያዘጋጅ ተገልጿል፡፡ እንደተለመደው ሁሉም የባለድርሻ አካላት በውይይቶች ላይ በመገኘትና ለፖሊሲ ጠቋሚ የሆኑ የመፍትሔ ሀሳቦችን በማመንጨት የነቃ ተሳትፎአቸው እንዲቀጥል አሳስበዋል፡፡ እስከአሁን የታየው ተሞክሮ ይኸ እንደሚሆን ያረጋግጥልናል ካሉ በኂላ «የጐዳና ህፃናት አጠቃላይ ሁኔታ በኢትዮጵያ» በሚል ርዕስ በዕለቱ የሚካሄደውን በ«ባህልና ልማት» ሥር አሥራ ሁለተኛና የመቋጫ የሆነውን የውይይት መድረክ ከፍተዋል፡፡

በእለቱ በአቶ አበባው በቀለ ለውይይት የቀረበው ጥናታዊ ፅሁፍ በዋነኛነት የጎዳና ህፃናት ፅንሰ ሀሳብ፣ የጎዳና ህጻናት ብዛትና ስርጭት፣ የጎዳና ህፃናትን የቤተሰብ፣ የእድሜና የጾታ ሁኔታ፣ የጎዳና ህይወት ገፅታዎች ለምሳሌ የአመጋገብ፣ የትምህርት፣ የጤና ሁኔታ፣ በጎዳና ተዳዳሪ ህፃናት ላይ የሚደርሱ ችግሮችና የሚቋቋሙባቸው መንገዶች በሚሉ ዋና ዋና ነጥቦች ላይ ያተኮረ ነበር፡፡ ጽሁፉ የጎዳና ላይ ህይወት ገፅታን በዝርዝር ይቃኛል፡፡ የጎዳና ህፃናቱን ችግር ለመታደግ መንግስታዊና መንግስታዊ ባልሆኑ ግብረ ሰናይ ድርጅቶች የተደረጉ ጥረቶችን በጥልቀት ዳስሷል፡፡ ለወደፊቱ ማህበረሰብንና ተቋማትን ወይም መዋቅርን መሰረት ያደረጉ ስራዎችን በመስራት የጎዳና ተዳዳሪ ህፃናትን ህይወት ለመታደግ ይበጃሉ ያሏቸውን የፖሊሲ ጠቋሚ የመፍትሄ ሀሳቦችንም ያቀርባል፡፡ አቶ አበባው የጎዳና ህፃናት ስለሚለው ፅንሰ ሀሳብ የተለያዩ ፍችዎችና አመለካከቶች መኖራቸውን ገልፀዋል፡፡ ለጥናታቸው መነሻ ይሆናቸው ዘንድ የተጠቀሙት አጠቃላይ የጎዳና ህፃናቱን ሁኔታና አኗኗር ይመለከታል፡፡ በአንድ በኩል አብዛኛው ጊዜአቸውን ጎዳና ላይ በስራ የሚያሳልፉ እና ሲመሽ ወደ ቤታቸው የሚመለሱ ህጻናትን ያጠቃልላል፡፡ በሌላ በኩል ውሎአቸውንና አዳራቸውን ጎዳና ላይ ያደረጉ ከ8-18 አመት እድሜ ክልል ውስጥ የሚገኙ ህፃናትን የሚሸፍን መሆኑን ገልፀዋል፡፡

በአለም ላይ ከ100-150 ሚሊዮን የሚደርሱ ህፃናት እንደሚኖሩ ይገመታል፡፡ ከዚህም ቁጥር አብዛኛዎቹ ገና በማደግ ላይ ባሉ ሀገራት የሚገኙ ናቸው፡፡ በሀገራችን ኢትዮጵያ የጎዳና ህፃናትን አስመልክቶ በተሟላ መልኩ የተጠናከረ መረጃ ማግኘት አስቸጋሪ ነው፡፡ በመሆኑም በተለያዩ ድርጅቶች የሚዘጋጁ ሪፖርቶች የጎዳና ህፃናቱን ቁጥር፣ብዛትና ስርጭት በተመለከተ በእጅጉ የተለያዩና የሚጋጩ መረጃዎችን ያቀርባሉ፡፡ ለምሳሌ በ1995 ዓ.ም በሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር በተደረገ ብሔራዊ የዳሰሳ ጥናት በኢትዮጵያ ውስጥ አንድ መቶ ሺህ የጎዳና ህፃናት እንደሚገኙ ይገልፃል፡፡ ከአንድ አመት በኃላ በተባበሩት መንግስታት ህፃናት መርጃ ድርጅት የወጣ ሪፖርት የጎዳና ህፃናቱን ቁጥር ወደ ሁለት መቶ ሺህ ከፍ ያደርገዋል፡፡ በሌላ በኩል የጎዳና ህፃናት ወዳጆች ማህበር በ2003 እ.አ.አ በስምንት ከተሞች ላይ ባደረገውን ጥናት የጎዳና ህፃናቱን ቁጥር አንድ መቶ ሺህ እንደሚሆን ያመለክታል፡፡ በሌላ መልኩ የአዲስ አበባ መስተዳዳር ሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮ በሐምሌ 2002 ዓ.ም ባደረገው ቆጠራ በከተማዋ ከአራት ሺህ በላይ የሚሆኑ ውሎአቸውንና አዳራቸውን ጎዳና ላይ ያደረጉ ህፃናት ስለመኖራቸው ተመልክቷል፡፡

በኢትዮጵያ የጎዳና ህፃናትን የእድሜና የጾታ ሁኔታ በተመለከተ የተለያዩ ጥናቶች የተለያዩ ውጤቶችን ያመላክታሉ፡፡ሆኖም በአብዛኛው የኢትዮጵያ ከተሞች የሚገኙ የጎዳና ህፃናት የእድሜ ክልል ከ13-15 አመት ባለው መካከል የሚገኙ መሆናቸው ነው የሚጠቀሰው፡፡ የሴት የጎዳና ህፃናት ቁጥርም ከ 30% የማይበልጥ መሆኑን አቶ አበባው ለተሰብሳቢዎቹ አስረድተዋል፡፡ የእነዚህን የጎዳና ህፃናት የቤተሰብ ሁኔታ በተመለከተ በከተማ እና በገጠር የሚገኙ እጅግ ድሀ ከሆኑና በትዳር ችግር ውስጥ ከሚኖሩ ቤተሰቦችና የተፈጥሮና ሰው ሰራሽ አደጋዎች ከሚጠቁ አካባቢዎች የሚወጡ መሆናቸው ታውቋል፡፡ አብዛኛዎቹም የጎዳና ህጻናት ከወላጆቻቸው ቢያንስ አንዱ በህይወት የለም፡፡በርካታ የሚሆኑት ከሌሎች አካባቢዎች ፈልሰው በስደት እንደመጡ የተለያዩ ጥናቶችን በዋቢነት በመጥቀስ አስረድተዋል፡፡ ከዚህ ጋር በማያያዝ በቤተሰብ ውስጥ በልጆች ላይ የሚፈፀሙ ድብደባዎችና አካላዊ ቅጣቶች፣የቤተሰብ መፍረስና የኑሮ





መናጋት፣ ለህፃናት ፍልሰትና የጎዳና ኑሮ ተጠቃሽ ምክንያቶች መሆናቸውንም አስገንዝበዋል፡፡

የጎዳና ህፃናት በአንድ ቦታ በቋሚነት የመኖር ባህሪ የላቸውም፡፡ በመሆኑም ለበርካታ ችግሮች ማለትም ለብርድ፣ ለፀሀይ፣ ለጉልበት ብዝበዛ ፣ለምግብ እጥረት ፣ለአደንዛዥ እፅ ፣ ለጥቃትና ለተለያዩ የጤና ችግሮች ይጋለጣሉ፡፡ ይሄም በተለያዩ ጥናቶች የተዘገበና እውቅና የተሰጠው ጉዳይ ነው፡፡ አቶ አበባው እንደጠቆሙት በኢትዮጵያ ከጠቅላላው የጎዳና ህፃናት ውስጥ 15% የሚሆኑት ውሎና አዳራቸውን ጎዳና ላይ ያደረጉ ናቸው፡፡ አብዛኛዎቹም በሚኖሩት የጎዳና ህይወት ላይ ደስተኛ አይደሉም፡፡ እጅግ በጣም ጥቂት የሚሆኑትም ትምህርታቸውን የሚከታተሉና የወደፊት አላማ ያላቸው መሆኑን ጠቁመዋል፡፡ በርካታ ጥናቶች እንደሚጠቁሙት የጎዳና ተዳዳሪ ህፃናት ራሳቸውን ከተለያዩ ጥቃቶች ለመከላከል በቡድን ይደራጃሉ፡፡ ቢሆንም በአብዛኛው በድብደባ ፣በወሲባዊ ጥቃትና በዘፈቀደ በመያዝና በመታሰር ይንገላታሉ፡፡ የህፃናቱን ችግር ከመቅረፍ አኳያ በተለያዩ መንግስታዊና መንግስታዊ ባልሆኑ ተቋማት በኩል በተናጠል የሚደረጉ የተለያዩ ጥረቶች ይስተዋላሉ፡፡ ሆኖም ግን ከችግሩ ስፋትና ጥልቀት አንፃር አባይን በጭልፋ እንደማለት ነው ብለዋል፡፡

እንደ አቶ አበባው ገለፃ በኢትዮጵያ ከ60 በላይ የሚሆኑ ግብረ ሰናይ ድርጅቶች በቀጥታ በጎዳና ህፃናት ላይ ትኩረት በማደረግ ተሰማርተዋል፡፡ አስቀድሞ የመከላከል፣ የማበረታታት፣ የድጋፍና እንዲሁም የመልሶ ማቋቋምና የተሐድሶ ፕሮግራሞችን ቀርፀው የሚንቀሳቀሱ መሆናቸውም ታውቋል፡፡ በመንግስት በኩል የህፃናት ደህንነት ጥበቃ እና ለችግር ተጋላጭ ለሆኑ ህፃናት በተወሰነ ደረጃም ቢሆን የተለያዩ የአቅም ግምባታና የድጋፍ ስራዎች ይሰራሉ፡፡ ይሁን እንጂ የጎዳና ተዳዳሪ ህፃናት ችግር በዘላቂነት ከመቅረፍ አኳያ የሚደረጉ ጥረቶች የሁሉንም የባለድርሻ አካላት ማለትም የመንግስትን፣ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን፣ የሀይማኖት ተቋማትን ፣የህብረተሰቡንና የግል ተቋማትን የተቀናጀ ጥረትና እንቅስቃሴ ይፈልጋሉ፡፡

አቶ አበባው በማጠቃለያቸው የጎዳና ህፃናትን ችግር ወጥነትና ዘላቂነት ባለው ሁኔታ ለመቅረፍ ያግዛሉ ያሉአቸውን የመፍትሄ ጠቋሚ የፖሊሲ ፍሬ ሀሳቦች ለውይይት አቅርበዋል፡፡ከእነዚህም መካከል በህግ አስፈፃሚ አካላት መዋቅር ውስጥ ለጎዳና ህፃናት ተስማሚ የሆኑ አሰራሮችና አገልግሎቶች እንዲኖሩ የማስቻል ስራን በተገቢው መስራት አንዱ ነው፡፡ በተጨማሪም የህፃናት ጥበቃ ክፍሎችና የህፃናት ማረሚያ ማዕከላት አብይ ሚና አላቸው፡፡ ከመንግስት አግልግሎት ሰጭ ተቋማት ጋር የጠበቀ የስራ ግንኙነት በመፍጠር አሰቻጋሪ ሁኔታ ውስጥ ያሉ የጎዳና ህፃናት ህክምናን ጨምሮ ለህፃናት አስፈላጊና መሰረታዊ የሆኑ አግልግሎቶችን የሚያገኙበትን ሁኔታ ማመቻቸት አሌ የማይባል ነው፡፡ የግንዛቤ ማስጨበጫና ተከታይ የአቅም ግምባታ ስራዎችንም መስራት ያስፈልጋል፡፡ በተጨማሪም ሁሉንም የባለድርሻ አካላት ያሳተፈ ማህበረሰብ አቀፍ የህፃናት ደህንነት ጥበቃ ስርአት በሁሉም የአስተዳደር ደረጃ መዘርጋት የሚሉት ይገኙበታል፡፡

በውይይቱ ላይ 90 የሚሆኑ የባለድርሻ አካላት ተገኝተዋል፡፡ ከተጋባዥ አስተያየት አቅራቢው ከአቶ ፋሲል ወ/ማርያም እንዲሁም ከታዳሚዎች ለውይይት ለቀረበው ጥናታዊ ፅሁፍ ማጠናከሪያ፣ ማዳበሪያ የሚሆኑና የመፍትሄ አቅጣጫ ጠቋሚ የሆኑ ሀሳቦች ቀርበዋል፡፡ ከእነዚህም መካከል የጎዳና ህፃናትን የዕድሜ ክልልና የቃሉን ፍቺ በተመለከተ በሁሉም ባለድርሻ አካላት መካከል የጋራ መግባባት ላይ መድረስ፣ እንደሚገባ፣ በተቋማት በኩል የሚደረጉ የእርዳታና የመልሶ ማቋቋም እንቅስቃሴዎች በጎዳና ህፃናቱ ሙሉ ፍቃደኝነትና ፍላጎት ላይ የተመሰረቱ መሆናቸውን ማረጋገጥ፣ የጎዳና ህፃናት የመስራት መብትና ለአግልግሎታቸውም ተገቢውን ክፍያና የህግ ጥበቃና ከለላ መስጠት የሚሉ ይገኙበታል፡፡ በጎዳና ህፃናት ላይ የሚደርስ የወሲብ ጥቃትን በተመለከተ በሴት ህፃናት ላይ ብቻ ሳይሆን በወንድ ህፃናቶችም ላይ የሚደርሰውን ጥቃት ግንዛቤ ውስጥ ማስገባት አስፈላጊ ነው፡፡ ከጎዳና ህፃናት ጋር በተያያዘ የሚሰሩ ስራዎችን ለመከወንና በተለይ የትምህርት፣የአቅም ግምባታና የተሐድሶ ስራዎችን ለማከናወን በመስኩ የጥናትና ምርምር ስራዎችን በተገቢው ማከናወን እንደሚገባ የሚጠቁሙ ይገኙበታል፡፡

# የአየር ንብረት ለውጥ፤ የውሃ ሐብትና የኢነርጂ ልማት በኢትዮጵያ

ፎረም ፎር ሶሻል ስተዲስ ‹‹የአየር ንብረት ለውጥ፤ የአካባቢ ጥበቃና ልማት በኢትዮጵያ›› በሚል ዐቢይ ርዕስ ያዘጋጀው ሰባተኛውና የመጨረሻው የውይይት መድረክ ‹‹የአየር ንብረት ለውጥ፤ የውሀ ሐብትና የኢነርጂ ልማት ትስስር በኢትዮጵያ›› በሚል ርዕስ መጋቢት 2 ቀን 2003 ዓ.ም በግዮን ሆቴል ተካሄዷል፡፡ ለዕለቱ ውይይት መነሻ የሆነውን ጥናታዊ ጽሁፍ ያቀረቡት በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የአካባቢያዊ ሳይንስ መርሀ-ግብር ዋና ዳይሬክተር የሆኑት ዶ/ር መኩሪያ አርጋው ናቸው፡፡

የእለቱን ውይይት የአካባቢ ተቆርቋሪዎች መድረክ ዳይሬክተርና በኢትዮጵያ በየአር ንብረት ዙሪያ የሚሰራው የሲቪል ማህበራት ጥምረት አስተባባሪ የሆኑ አቶ ንጉሱ አክሊሉ በአወያይነት የመሩት ነበር፡፡ ለውይይት በቀረበው ጽሁፍ ላይ አቶ ጌዲዮን አስፋው ሙያዊ አስተያየታቸውን ሰጥተዋል፡፡ አቶ ጌዲዮን በአካባቢ ጥበቃና ተፈጥሮ ሀብት ልማት ዙሪያ ለበርካታ አመታት የሰሩና ልምድ ያካበቱ ሲሆን በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገራት በመስኩ በተለያዩ የሀላፊነት ደረጃዎች የሠሩ አንጋፋና ዕውቅ ባለሙያ ናቸው፡፡ ይህ ስብሰባ ፎረም ፎር ሶሻል ስተዲስ ከየካቲት 2002 - መጋቢት 2003 ለአንድ አመት ያህል በተከታታይ ሲያዘጋጃቸው ለነበሩት የውይይት መድረኮች የመቋጫ ውይይት ነበር፡፡ በእለቱ ውይይትና በመዝጊያው በአል ላይ ጉዳዮ የሚመለከታቸው መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ አካላት ተወካዮች እንዲሁም የኤፍ ኤስ ኤስ አባላት፤ ደጋፊዎችና ተመራማሪዎች በብዛት ተገኝተዋል፡፡

የፎረም ፎር ሶሻል ስተዲስ ሥራ አስፈፃሚ ዳይሬክተር ዶ/ር ምህረት አየነው አመታዊ የውይይት መርሀ-ግብሩን የመዝጊያ ንግግር አድርገዋል፡፡ እሳቸውም እንደገለፁት ኤፍ ኤስ ኤስ ከተቋቋመት ከ1990 ዓ.ም ጀምሮ በተፈጥሮ ሀብትና በአካባቢ ልማት ጉዳዮች ዙሪያ ፈርጀ ብዙ ፋይዳ ያላቸውና ለፖሊሲ ግብአት የሚውሉ የተለያዮ የምርምር ሥራዎችን ሲያከናውን እንደቆየ አስገንዝበዋል፡፡ የህዝባዊ የውይይት መድረኮችን በማዘጋጀትም ጉዳዩ የሚመለከታቸውን አካላት አወያይቷል፤ የምርምርና የውይይት ውጤቶቹንም በስፋት አሰራጭቷል፡፡ በተለይ በህዝባዊ ውይይት ዙሪያ የአካባቢ ልማትና የአካባቢ ለውጥ ጉዳዮች፤ የአካባቢ ጥበቃ የድህነትና የሴቶች ጉዳይ፤ የአካባቢ ጥበቃ ክፍተቶችና የተፈጥሮ ሀብት

ግጭቶች፤ የኢኮኖሚ ልማት ተፅእኖ በአካባቢ ጉዳዮች ዙሪያ፤ የመንግስት የአካባቢ ጥበቃ ፖሊሲ፤ የግልና የጋራ ጥረት ለአካባቢ ህይወት መሻሻል (የሰሜን ሸዋ ገበሬዎች ተሞክሮ)፤ በኢትዮጵያ የተደቀኑ የአካባቢና የተፈጥሮ ሀብት ልማት ፈተናዎችና የሀገር በቀል ዛፎች ሚና ዙሪያ የቀረቡ ጉዳዮች ነበሩ፡፡ በምርምር መስክ ደግሞ በከሰል ፍጆታና በአካባቢ ጤና ጠንቆች፣ በውሃ ማቆርና የዝናብ ውሀ ማስባስብ እንዲሁም በአየር ንብረት ለውጥ ተፅእኖ እና የማጣጣም ሂደት ዙሪያ የተከናወኑትን በምሳሌነት አውስተዋል፡፡




ዶ/ር ምህረት በተጨማሪያም ለውይይቱ ተሳታፊዎች እንዳስገነዘቡት ኤፍ ኤስ ኤስ የአየር ንብረት ለውጥ ጉዳዮች ላይ የምርምርና የህዝባዊ የውይይት መድረኮችን ለማዘጋጀት ሲወስን የአየር ንብረት ለውጥ እየከፋና እየተባባሰ የሚሄድ ዋነኛ የልማትና የዘላቂ ለውጥ ችግሮች መሆኑን በመረዳት ነው፡፡ የኢትዮጵን የአየር ንብረት ለውጥ ተጋላጭነት በመገንዘብ ከለውጡ ጋር ተጣጥሞ መሄድ የሀገሪቱን የወደፊት የዕድገት ደረጃ ከሚወሰኑት ጉዳዮች አንዱና ዋነኛው እንደሆነ አያጠያይቅም፡፡ ከዚህ አንፃር የአየር ንብረት ለውጥና የአካባቢ ጥበቃ ጉዳዮች በ5 ዓመቱ የልማትና የዘላቂ ለውጥ እቅድ (GTP) ላይ ትኩረት ማግኘታቸው መልካም ጅምርና እሰየው የሚባል እንደሆነ አብራርተዋል፡፡ እቅዱን ለማስፈጸም የሚዘጋጁት ስትራቴጅዎችና ለማጣጣም የሚደረጉ ጥረቶች በሙሉ ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር ኢኮኖሚንና ማህበረሰብን ከመገንባት አንፃር የሚቃኙ መሆናቸውን መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡ የማጣጣምና የስርዮት (mitigation) ስራዎች በጥናትና ምርምር እንዲታገዙም ያስፈልጋል፡፡ ከአካባቢ ዕውቀቶችና ጠቃሚ ልምዶች ጋር የተወዳጁ መሆኑ ለውጡን ለመቋቋም ተገቢውን ሀገራዊ አቅም ከመገንባትና ከማጎልበት ባሻገር ከንፁህ የልማት ስርዓቶችና (Clean Development Mechanisms) ከአየር ንብረት ለውጥ የማጣጣሚያ የድጋፍ የገንዘብ ቋት (Adaptation fund) ተጠቃሚ የምንሆንበትን ሁኔታ ለማመቻቸት እንደምንችል እምነታችን ነው ብለዋል፡፡

በመጨረሻም ኤፍ ኤስ ኤስ ከዚህ ጠቃሚ ልምዱ በመነሳት በቅርቡ ሌላ አዲስ የምርምርና የህዝባዊ የውይይት መድረክ በተለይ በአየር ንብረት ለውጥና በውሀ ሀብት ልማት ዙሪያ ለማካሄድ በዝግጅት ላይ መሆኑን በመግለፅ የሁሉም የባለድርሻ አካላት እገዛና ተሳትፎ እንደሚቀጥል እምነታቸው መሆኑን በመግለፅ የዕለቱን ውይይት ከፍተዋል፡፡

በዶ/ር መኩሪያ አርጋው ለውይይት የቀረበው ጥናታዊ ፅሁፍ ብዙ ጉዳዮችን አካቷል፡፡ በዋነኛነት የኢትዮጵያ የውሀ ሃብት ይዘትና ሁናቴ ፤ ዋና ዋና የሀይል ምንጮች፤ የውሀና የሀይል ምንጮች ጥብቅ ትስስር፤ የአየር ንብረት ለውጥ ዳሰሳ፤ የአየር ንብረት ለውጥ ተፅእኖ በውሀ ልማትና በሀይል አቅርቦት ዙሪያ፤ የአየር ንብረት ለውጥ ተፅእኖን ለመቋቋም የሚረዱ ጉዳዮችን ያጠቃልላል፡፡ ለውጡን ከልማት ጋር ለማጣጣም የተዘጋጁ ፖሊሲዎች አጭር ዳሰሳና ለወደፊቱ ለማጣጣምና ስርዮት (mitigation) ስራ የሚበጁ የፖሊሲ ጠቋሚ የመፍትሄ ፍሬ ሃሳቦች በሚሉ ዋና ዋና ክፍሎች የተከፋፈለ ነበር፡፡ አቅራቢው የአየር ንብረት ለውጥ የውሀና የሀይል አቅርቦት ዙሪያ የሚፈጥራቸውን ጫናዎች ለመገደብና ከለውጡ ጋር የሚጣጣሙ የውሃና የሃይል ምንጭ የልማት ስራዎችን ለማስፋፋት ይበጃሉ ያሉአቸውን የፖሊሲ ጠቋሚ የመፍትሄ ሃሳቦች በመጠቆም ይደመድማል፡፡

ኢትዮጵያ በተፈጥሮ በውሃ ሀብት የታደለች ሀገር መሆኗ ይታወቃል፡፡ ያላትን ሰፊ የውሃ ሀብት በጥንቃቄ ለመያዝና ዘላቂነት ባለው መልኩ ለመጠቀም ቢቻል ለሀገሪቱ የኢኮኖሚ ዕድገት የውሀው ሀብት የሚኖረው ድርሻ እጅግ ከፍተኛ ነው፡፡ይሁን እንጂ ሀገሪቱ ካላት ጠቅላላ የውሀ ሀብት (123 Bm3/ year) ከፍተኛ የሆነው 97% ከሀገር ውጭ የሚፈስ ሲሆን በሀገር ውስጥ ከሚቀረው 3% ጥቅም ላይ ለማዋል የተቻለው ከ 5% አይበልጥም፡፡ በመስኖ መልማት ከሚችለው 3.7 ሚሊዮን ሄክታር መሬት ለማልማት የተቻለው 300,000 ሄክታር ብቻ ነው፡፡ ለሀይል ማመንጫ መዋል ከሚችለው ወደ 45,000 mw ለመጠቀም የተቻለው ከ 5% ያነሰ ነው፡፡ በዚህ ላይ በውሀ አካላት ከፍተኛ የሆነ የትነትና የብክለት መጠን ይታያል፡፡ በአማካይ ካለው የውሃ አቅርቦት የብክነት መጠኑ ከ20-25% ይሆናል፡፡ የንፁህ መጠጥ ውሃ አቅርቦት 36% ሲሆን ከሰሀራ በታች ባሉ ሀገራት ደረጃ እንኳን ሲታይ ዝቅተኛው ነው፡፡

እንደ ዶ/ር መኩሪያ ገለፃ በኢትዮጵያ የሀይል አቅርቦት የአንበሳውን ድርሻ ወይም እስከ 94% የሚደርሰውን የሚይዘው



ከእፀዋትና እፅዋት ነክ የሚገኘው የሀይል ምንጭ ነው፡፡ እ.አ.እ በ2009 የነበረው የሀይል አቅርቦት በአማካይ በነፍስ ወከፍ 42kwh ብቻ የነበረ ሲሆን ይህም ከሰሀራ በታች ካሉ ሀገራት አማካይ 126 kwh ጋር ሲነፃፀር ዝቅተኛው ነበር፡፡ ምንም እንኳን የሀይል ብክነትን ባለፉት አመታት ለመቀነስ ቢቻልም ለምሳሌ እ.አ.እ በ2002 ወደ 22% የነበረውን በ2007 እ.አ.አ ወደ 19.5% መቀነስ ተችሏል ብለዋል፡፡

ዶ/ር መኩሪያ የአየር ንብረት ለውጥ በውሀ ሀብት ላይ የሚያሳድረውን ተፅእኖ ሲያስረዱ በአጠቃላይ የአየር ንብረት ለውጥ ማለት የውሀ ሀብት ለውጥ ማለት ነው፡፡ በተለይ እንደ ኢትዮጵያ ባሉ ድሀ ሀገራት ለውጡን ተከትሎ የሚከሰት ድርቅና የሙቀትና የትነት መጨመር የውሀ አካላትን ይዞታና የፍሰት መጠን ያውካል፡፡ በኢኮኖሚና ሰብአዊ ልማት ላይ ከፍተኛ የሆነ አሉታዊ ተፅእኖን ያሳድራል፡፡ በሌላ በኩል የአየር ንብረት ለውጥ በውሀ አካላትና በእፅዋት ላይ በሚያሳድረው ተፅእኖ የተነሳ በዘመናዊም ሆነ ባህላዊ የሀይል ምንጮችና አቅርቦት ላይ የሚያሳድረው ተፅእኖ ቀላል አይሆንም፡፡



እንደ ዶ/ር መኩሪያ ገለፃ ከ 1991 ዓ.ም ጀምሮ የውሀ ሀብት ልማትና የሀይል አቅርቦትን ለማስፋፋት በመንግስት በኩል የተለያዩ አበረታች የሆኑ የፖሊሲ እርምጃዎች ተወስደዋል፡፡ ከእነዚህም መካከል በተለይ በውሃ ሀብት ልማት መስክ የወጡ ፖሊሲዎችና ስትራቴጅዎች የተፋሰስ ልማትንና የውሀ ምንጮችን በማጎልበትና በመንከባከብ የውሀ ምርትን ጥራትን በማሳደግ ላይ ተገቢውን ትኩረት ይሰጣሉ፡፡ በኢነርጂ ልማት በኩልም ስነ-ምህዳርንና አካባቢን በጠበቀ መልኩ የደን ልማትንና የውሀ ምንጭ ማጎልበትና የውሀ ማሰባሰብ ስራን ማስፋፋት ተችሏል፡፡ በዚህም ሳቢያ የሀይል አቅርቦቱን ቀስ በቀስ ለማሳደግና ከባህላዊ የእፅዋት አጠቃቀም ወደ ዘመናዊ የኤሌክትሪክ ሀይል ምንጭ ለመቀየር ትኩረት ተደርጓል፡፡ ምንም እንኳን በውሀ ልማትና በሀይል አቅርቦት በኩል ከፍተኛ የሆነ የፖሊሲ ማሻሻያ በተግባርም ለውጥ የተመዘገበ ቢሆንም በተግባር ከፍተኛ ክፍተት መኖሩን አስገንዝበዋል፡፡ በፖሊሲ ደረጃም ቢሆን በተለይ የውሃንና የሀይል ልማት ቁርኝቱን ፥ ሥነ-ምህዳራዊ የተፋሰስ ልማትንና የደን ሀብት ልማት ለውሀ የሀይል ልማት ያለውን ቁልፍ ሚና ክፍተት መኖሩንና በዚህ በኩል ከፍተኛ ስራ የሚጠብቀን መሆኑን ዶ/ር መኩሪያ አልሸሸጉም፡፡

ዶ/ር መኩሪያ በማጠቃለያቸው የውሀ ሀብትና የሀይል ምንጭ ልማትን በቁርኝት ማስኬድ አስፈላጊ መሆኑን አስገንዝበዋል፡፡በተለይም ሁለቱም ለአየር ንብረት ለውጥ ያላቸውን ተጋላጭነት በመቀነስና ከለውጡ ጋር በማጣጣም በሀገሪቱ ያለውን ዕምቅ ሀብት ልማት ላይ ለማዋል ያግዛሉ ያሉአቸውን የመፍትሄ ጠቋሚ የፖሊሲ ፍሬ ሀሳቦች ለውይይት አቅርበዋል፡፡ ከእነዚህም መካከል ኢትዮጵያ የአየር ንብረት ፖሊሲ እንደሚ|ስፈልጋት፥ ሥነ-ምህዳርን መሰረት ያደረገ የማጣጣም ስራን አስፈላጊነት፥ በውሃ ሀብትና የሀይል ምንጭ ልማት ዙሪያ የሚሰሩ ተቋማት ተቀናጅተውና ተቀራርበው ለተፋሰስ ልማት ልዩ ትኩረት ሰጥተው መስራት እንደሚጠበቅባቸው፥ በንጹህ የልማት ስርዓት (Clean Development Mechanisms) ተጠቃሚነትን በማሳደግ በተለይ በህላዊ የመሬት አጠቃቀምና የተቀናጀ የተፋሰስ ልማት ላይ ትኩረት ሰጥቶ መስራት ይገባል ብለዋል፡፡ በተለይ ድንበር ተሻጋሪ የውሀ አካላት ላይ የልማትና የማጣጣም ስራን ለመከወን የክፍለ ቀጠናዊ ትብብር አስፈላጊነትን የሚጠቁሙ አስተያየቶችም ቀርበዋል፡፡

በውይይቱ ላይ 90 የሚሆኑ የባለድርሻ አካላት ተገኝተው ነበር፡፡ ከእለቱ አስተያየት አቅራቢ አቶ ጌዲዮን አስፋው እንዲሁም ከታዳሚዎች ለውይይት ለቀረበው ጥንታዊ ፅሁፍ ማጠናከሪያ፣ ማዳበሪያና የሚሆኑና የመፍትሄ አቅጣጫ ጠቋሚ ሊሆኑ የሚችሉ የተለያዩ ሀሳቦች ቀርበዋል፡፡ ከእነዚህ መካከል በዘላቂ የመሬት አጠቃቀምና ተፋሰስን መሰረት ያደረገው የልማት ስትራቴጅ በስፋትና በተጠናከረ መልኩ ቢተገበር ለማጣጣም ስራው ከፍተኛ አስተዋፅኦ እንደሚኖረው፥ ተሰምሮበታል፡፡ በታዳሽ የሀይል ምንጮች ዙሪያ በምርምር በመታገዝ ሰፊ ስራን መስራት ቢቻል በውሃ ሀብት ላይ ያለውን ጥገኝነት ሊቀንስው ይችላል፡፡ የደን ሀብት ልማት ላይ በስፋት መንቀሳቀስ ለውሃ ሀብትም ሆነ ለሀይል ልማት ዋስትና እንደሚሆን፥ በአየር ንብረት ለውጥና በሀይል ምንጭ ልማት ዙሪያ ዝርዝር ጥናቶች እንደሚያስፈልጉና በጥናቱ የቀረቡ አንዳንድ አሀዛዊ መረጃዎች የቆዩ ስለሚመስሉ በቅርብ አመታት ከወጡ መረጃዎች ጋር ማገናዘብ እንደሚገባ የሚጠቁሙም ይገኙበታል፡፡





# የፎረም ፎር ሶሻል ስተዲስ አመታዊ ጠቅላላ ጉባኤውን አካሄደ

የፎረም ፎር ሶሻል ስተዲስ መጋቢት 3 ቀን 2003 ዓ.ም. እና ሚያዝያ 1 ቀን 2003 ዓ.ም. ባደረጋቸው ሁለት ተከታታይ አመታዊ ጠቅላላ ጉባኤዎች የተለያዩ ውሳኔዎች አሳልፏል፡፡ ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ነበሩ፡-

- የድርጅቱን እኤአ 2010 የአመቱ የስራ ክንውን ሪፖርት ፀድቋል፡፡
- ለሁለት ተከታታይ የስራ ዘመን በቦርድ አባልነት በማገልገል የስራ ዘመናቸውን በአጠናቀቁት አራት አባላት ምትክ ሌሎች አዲስ የቦርድ አባላት እንዲገቡ ተደርጓል፡፡
- የድርጅቱ እ.አ.አ 2011 የስራ እቅድ ሊገኝ የሚችለው በጀት በውል ባለመታወቁ ምክንያት በስራ አስፈፃሚ ዳይሬክተሩ አማካኝነት በጥቅሉ ከቀረበ በኋላ አስተያየቶች ተሰጥተውበታል፡፡ የተሰጡትን አስተያየቶች በማጠናቀርና ሊገኝ የሚችለውን በጀት ግምት ውስጥ በማስገባት በስራ አስፈፃሚና በቦርዱ ተጠናክሮ እንዲዘጋጅ ውሳኔ ላይ ተደርሷል፡፡
- እአአ 2010 የድርጅቱ የኦዲት ሪፖርት በኦዲተሮች ከቀረበ በኋላ ጉባኤው በሙሉ ድምጽ ተቀብሎታል፡፡
- የድርጅቱ ሕገ ደንብ በሚያዘው መሰረት መስፈርቶችን ያሟሉና በቦርዱ ቀደም ብለው ጉዳያቸው የፀደቀላቸው 5 አዳዲስ አባላት እንዲገቡ ጉባኤው ወስኗል








**FSS Update**

**Send your contributions to:**

**fss@ethionet.et**

# National Workshop on Urban Climate Change

ENDA-Ethiopia and the Ethiopian Civil Society Network on Climate Change organized a one-day workshop under the theme 'The Challenge of Climate Change and the Need for Adaptation in the Urban Areas of Ethiopia'. The workshop was held on 4 May 2011 at the Axum Hotel here in Addis Ababa; and focused on an assessment study conducted by ENDA-Ethiopia in 4 major urban areas----Addis Ababa, Dire Dawa, Bahir Dawa and Hawassa. The workshop brought together 30 representatives from relevant Government Ministries, Civil Society Organizations, and research institutions. A brief summary of the issues discussed during the workshop is given below.

Urban settlements in Ethiopia will be home to millions of additional residents, many of whom are likely to be stressed by uncertain conditions with regard to food and water availability, urban sanitation and health, education and employment opportunities. Climate change will constitute an added burden on these areas. However, most of the studies done so far on the linkages between climate change and development in Ethiopia are rural focused. Floods, heavy rainstorms, damaging winds as well as droughts are the most important climate related hazards in the four urban centers studied. Flood in particular has been a recurrent problem and it has caused loss of lives and property in Addis Ababa and Dire Dawa. For instance, in Addis Ababa 1,300 people were affected, 40 people were reportedly killed and 21 people were injured due to flooding in 1998. In Dire Dawa, flooding is a common phenomenon, and its frequency and extent of damage has increased in recent years. A flood incidence in May 2005 cost the lives of 35 persons and damaged property estimated at 10 million Birr. The 2006 flood was the worst in that 256 people were killed, 244 remained missing and

10,000 people were displaced.

Besides human health and economic impacts, floods are known to have a range of social and environmental consequences. The social impacts include displacement and disruption of household livelihoods and erosion of social capital. In addition, floods cause displacement of people in large numbers; damage houses and household belongings and infrastructure such as roads, bridges, schools; and disrupt agricultural production. Environmental consequences include stream bank erosion and channel modification, and damage to trees, shrubs and grasses along stream courses in addition to destroying environmental conservation works like soil and water conservation measures.

With regard to droughts, impacts are largely felt on shortage of energy and water supplies, food scarcity y in markets and high prices. Social and environmental sanitation problems related to the influx of drought victims from rural to urban areas are also observable. For example, in the case of Bahir Dar, the decline in Lake Tana levels affects its use for commercial transportation as well as for tourism and recreational activities. In the 2002/03 drought, the level of Lake Tana was reduced significantly, and this cost the Lake Tana Transport Enterprise over Birr 4,207,202. The vulnerability of the urban poor to the impacts of climate change is further compounded by the presence of multiple stressors including urban poverty, shortage of urban infrastructure and municipal services, and environmental pollution. There are complex and strong forward and backward linkages between the endemic urban problems in Ethiopian cities and towns caused by the added burden of climate change.

After long and thorough deliberations based on the assessment study, workshop participants put forward the following recommendations:

- Complementing structural measures that have been constructed along the river course in Dire Dawa by land use zoning and establishment of buffer zones;
- Resettling people from high-risk, flood-prone parts of Dire Dawa and Addis Ababa to safer areas;
- Establishing responsive flood-early warning system and real-time information sharing between upstream and downstream communities.
- Conserving upstream areas.
- Utilizing efficiently water resources, including roof water harvesting to augment urban water supply.
- Promoting urban development in terms of housing, infrastructure and provision of services has adaptation benefits.
- Improving climate change governance: linking local initiatives with national plans.
- Putting in place appropriate by-laws for urban planning, traffic, infrastructure and building
- Enhancing environmental law enforcement capacity
- Involving key stakeholders, such as NGOs, Donors, CBOs and the private sector in efforts to mitigate the adverse impact.
- Aggressively investing in urban green infrastructure
- Introducing pro-poor and inclusive environmental sensitive planning
- Implementing better transport and spatial planning
- Developing and implementing municipal adaptation strategy for each town. Such a strategy should give particular attention to the most vulnerable sectors and social groups.

# UN Climate Talks (Bangkok, 3-8 April 2011)

Under the United Nations Climate Change Negotiations, the sixteenth session of the Ad Hoc Working Group on Further Commitments for Annex I Parties under the Kyoto Protocol (AWG-KP 16), the fourteenth session of the Ad Hoc Working Group on Long-Term Cooperative Action (AWG-LCA 14), and three pre-sessional workshops convened in Bangkok, Thailand, from 3-8 April 2011. Parties converged on Bangkok for the first UNFCCC meeting following the adoption of the Cancun Agreements at the sixteenth Conference of the Parties (COP 16) in Mexico. Over 2000 participants from governments, intergovernmental and non-governmental organizations, academia, the private sector and the media attended the meetings. This marked the first round of negotiations on climate change following the sixteenth Conference of the Parties (COP 16), held in Cancun, Mexico in November - December 2010. Delegates set out to adopt the agenda and organization of work for 2011 to enable the Ad Hoc Working Groups to achieve their mandates in the lead up to the Conference of Parties (COP 17), to be held in December 2011 in Durban, South Africa.

### *Opening ceremony*

The Executive Secretary of the United Nations Framework Convention on Climate Change, Mrs. Christiana Figueres opened the UN Climate Change Conference, with a moment of silence for the victims of the earthquake and tsunami in Japan. She called for an atmosphere of compromise and said much work remained to be done, despite breakthroughs in Cancun (Mexico), and that full implementation of the Cancun Agreements is only one step towards addressing climate change. Noeleen Heyzer, Executive Secretary, United Nations Economic and Social Commission for Asia and the Pacific (UNESCAP), called on parties to renew their sense of urgency to tackle the increasingly adverse impacts of climate change on developing countries. She highlighted the importance of: risk reduction measures; building resilient societies; and pursuing a regional

approach to low carbon green growth. Suwit Khunkitti, Minister of Natural Resources and Environment, Thailand, said the Cancun pledges are inadequate to prevent the adverse effects of climate change. He urged developed country parties to take the lead on emission reductions and stressed that COP 17 must deliver the promised financial and technological support to developing countries to achieve their adaptation and mitigation targets.

On Sunday, 3 April, a pre-sessional workshop on assumptions and conditions related to the attainment of quantified economy-wide carbon emission reduction targets by developed country parties convened to discuss presentations and submissions by parties. On Monday, 4 April, a pre-sessional workshop on mitigation actions submitted by developing country parties, underlying assumptions, and any support needed for implementation of these actions discussed presentations and submissions by parties. The expert workshop on the Technology Mechanism took place from 4-5 April and focused on means of operationalizing the institutions of the Technology Mechanism, including the Technology Executive Committee (TEC) and the Climate Technology Centre and Network (CTCN).

AWG-LCA 14 and AWG-KP 16 convened from 5-8 April. The AWG-LCA opened with discussions on the agenda for the meeting, but parties could not reach agreement on whether to work on the basis of the agenda proposed by the AWG-LCA Chair or the one proposed by the Group of 77 and China (G-77/China). The group working on Long Term Cooperative Action met all week in informal consultations, informal plenaries and drafting groups to resolve the impasse. The group working on the Kyoto Protocol met three times in a contact group on further commitments for Annex I (developed country) parties and debate focused on how to address the political and technical issues that must be resolved in order to reach agreement on a second

Going forward to Durban in December 2011, the modest but critical achievements of the Bangkok meeting promises to release business-like efforts to concentrate on the detailed implementation of the Cancun Agreements, while suspending some of the pressure to conflate technical and political issues and fight proxy battles over agendas. The long-term journey that negotiators must take to bridge their current collective efforts and the demands of a global temperature goal, however, is less clear. The parties have reached a "crossroads" marked by the achievements, albeit insufficient, of Cancun. Given the increasing interdependence of the parties and groups when it comes to helping each other understand and address assumptions, conditions and rules behind their targets and goals, the current crossroads afford a moment to step back from the heightened intensity that has accompanied negotiations in the run-up to and since Copenhagen. In the incremental development of the climate change regime, there is an increasing need for parties and groups across the spectrum to institutionalize the integral link between levels of ambition and cooperation.

As the wisdom of Thailand's Buddhist teachers might observe: it is always wise to pause and take a moment to release or drop the frantic drive to control, calculate and uphold positions that have been useful up to a point (even in negotiations). This seems an appropriate lesson for the coming and demanding period of reorienting negotiations marked by modest achievement and beckoning ambition.

## *A brief history of the UNFCCC and the Kyoto Protocol*

The international political response to climate change began with the adoption of the United Nations Framework Convention on Climate Change (UNFCCC) in 1992, which sets out a framework for action aimed at stabilizing atmospheric concentrations of greenhouse gases to avoid "dangerous anthropogenic interference" with the climate system. The UNFCCC entered into force on 21 March 1994 and now has 195 parties.

In December 1997, delegates to the Conference of Parties (COP) 3 in Kyoto, Japan, agreed to a Protocol to the UNFCCC that commits industrialized countries and countries in transition to a market economy to achieve emission reduction targets. These countries, known as Annex I parties under the UNFCCC, agreed to reduce their overall emissions of six greenhouse gases by an average of 5.2% below 1990 levels between 2008-2012 (the first commitment period), with specific targets varying from country to country. The Kyoto Protocol entered into force on 16 February 2005 and now has 193 parties.

In 2005, COP/MOP 1, held in Montreal, Canada, established the Ad Hoc Working Group on Further Commitments for Annex I Parties under the Kyoto Protocol (AWG-KP) on the basis of Protocol Article 3.9, which mandates consideration of Annex I parties' further commitments at least seven years before the end of the first commitment period. In addition, COP 11 agreed in Montreal to consider long-term cooperation under the Convention through a series of four workshops known as "the Convention Dialogue," which continued until COP 13.

In 2009, COP 15 was held in Copenhagen, Denmark, from 7-19 December 2009. Over 110 world leaders attended the meeting. The conference was marked by disputes over transparency and process. During the high-level segment, informal negotiations took place in a group consisting of major economies and representatives of regional and other negotiating groups. Late in the evening of 18 December, these talks resulted in a political agreement, the "Copenhagen Accord". Delegates debated the Accord at length, with many supporting its adoption as a step towards securing a "better" future agreement, while others opposed it due to the lack of transparency in the process. Ultimately, parties agreed to "take note" of the Copenhagen Accord. They also established a process for parties to indicate their support for the Accord. To date, over 140 countries (including Ethiopia) have indicated their support. More than 80 countries have also provided information on their emission reduction targets and other mitigation actions.

In 2010, COP 16 took place in Cancun, Mexico, from 29 November to 11 December 2010 with over 12,000 participants. Expectations for Cancun were modest, with few anticipating a legally-binding outcome on all outstanding issues and therefore parties focused on identifying elements of a "balanced package" of outcomes. Negotiations focused on key issues including mitigation, adaptation, financing, technology, and international consultation and analysis (ICA). The conference was closed with the formation of the "Cancun Agreements." The Agreements included decisions under both the Convention and Protocol negotiating tracks and contained provisions on adaptation, technology, mitigation and finance.

In December 2011, COP 17 will be held in Durban, South Africa.